አርበኛ ለወያኔ
ተማሪው ጠላትህ፤ መምህሩ ጠላትህ
ምሁሩ ጠላትህ፤ መሀይሙ ጠላትህ
ነጋዴው ጠላትህ፤ ገበሬው ጠላትህ
ሠርቶ አደር ጠላትህ፤ ሥራ አጥ ጠላትህ
አርቲስቱ ጠላትህ፤ ደራሲው ጠላትህ
ጋዜጠኛው ጠላትህ፤ አንባቢው ጠላትህ
ሾፌሩ ጠላትህ፤ ተጓዡ ጠላትህ
ፖሊሱ ጠላትህ፤ ፓይለቱ ጠላትህ
እስረኛ ጠላትህ፤ ዳኛ ጠላትህ
አበሻ ጠላትህ፤ ኢትዮጵያ ጠላትህ
ተጠየቅ ወያኔ፤ ማን ይሆን ወዳጅህ?

ወያኔ ለአርበኛ
ዘረኛ ወዳጄ፤ ሆድ አደር ወዳጄ
ከሀዲው ወዳጄ፤ ውሸታም ወዳጄ
ጎሰኛ ወዳጄ፤ ባንዳ ወዳጄ
አርበኛ የተባለ፤ አያልፍም በደጄ
በራሴ ጥቅም ላይ፤ አላውቅም ቀልጄ
የአበሻን ባንዲራ፤ ጥዬ ቀዳድጄ
ታሪኩን አርክሼ፤ ባጭር ቆራርጬ
እንደ ቅርጫ ሥጋ፤ ክፍልፍል አድርጌ
ኦሮሞን ከአማራ፤ ትግሬን ከጉራጌ
ቀስፌ ይዣችሁ፤ በራስጌ በግርጌ
በአጋዚ ጦሬ፤ ታጥሬ መሽጌ
ገና እገዛለሁ፤ ምን አይታችሁ ገና
ሥልጣን በቀላሉ፤ አይገኝምና፡፡

ወ/ሮ ኢትዮጵያ ለወያኔ
ሥልጣን  በቀላሉ፤ አይገኝም ያልከው
እውነት አይመስለኝም፤ ጨርሶ ውሸት ነው
ደርጉ ሲፈረጥጥ፤ ዘለህ የገባኸው
አሸንፈህ ሳይሆን፤ ልጆቼ ፈቅደው ነው
እረስተህ እንደሆን፤ ማስታወስ ጥሩ ነው
ከቶም አትሳሳት፤ ሥልጣኑ የኔ ነው፡፡
(ከማህሉ በቀለ)